የሰ/መ/ቁ/21389

ቀን 13/7/98 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሃይ ታደሠ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ ጌታቸው ምህረቱ

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- ስለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

- ነ/ፈጅ አያሌው አለማየሁ - ቀርበዋል

መ/ሰጭ፡- አቶ ፈቃዱ አካሉ - ቀርበዋል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በድሬዳዋ አሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከፈለው በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቦርዱም ግራ-ቀኙን አከራክሮ በ6/5/89 በዋለው ችሎት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም ከዚሁ ውሳኔ በኂላ በአመልካች በኩል የቀረበለትን የውሳኔ ይታረምልኝ ማመልከቻ ተቀብሎ መጀመሪያ ሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ በማረም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም ለድሬዳዋ ፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ቦርዱ ሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካችም በፍ/ቤቱ ውሣኔ የተፈጸመ የሕግ ስህተት አለ በማለታቸው ውሣኔው እንዲታረም ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 13-10-98

አቅርበው ችሎቱ በ21/9/95 በዋለው ችሎት በሠጠው ውሳኔ ቦርዱ የግራ-ቀኙን የመደመጥ መብት ሊጠብቅ የሚገባ በመሆኑ በእርምት አቤቱታው ላይ ግራ-ቀኙን አስቀርቦ ይወሰን በማለት ጉዳዩን ለቦርድ መልሶታል፡፡

ቦርዱም በችሎቱ በተሠጠው መመሪያ መሠረት የውሳኔ ይታረምልኝ አቤቱታው ለተጠሪ እንዲደርስ በማድረግ ግራ-ቀኙን አከራክሮ የተጠሪን የደሞወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ይከፈለኝ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ተጠሪም በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ በመጠየቁ ይግባኙ የቀረበለት የድሬዳዋ ፌ/ከ/ፍ/ቤት ቦርዱ በሰበር ሰሚው ችሎት የታዘዘው ተፈፅሞ የነበረ የስነ-ስርዓት ግድፈትን እንዲያርም እንጂ በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ ዋናውን ጉዳይ አርሞ ውሳኔ እንዲሠጥ አይደለም በማለት ቦርዱ ቀድሞ በፍሬ-ጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሣኔ ማረም ሣያስፈልገው መዝገቡን እንዲዘጋ ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን የሰበር ችሎቱም ቦርዱ ውሣኔ የሠጠው የሠበር ችሎቱ ከሠጠው መመሪያ ውጪ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር መዝገቡን አስቀርቦ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል፡፡

ምንም እንኳን ይህ መዝገብ የተለያዩ የፍርድ ሂደቶችን ያለፈ ቢሆንም ለአሁኑ የሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ቀደም ሲል ይህ ችሎት በ21/9/95 ዓ.ም በሠጠው ውሣኔ ጉዳዩን በመመሪያ ለቦርድ በመመለሱና ቦርዱም በተሠጠው መመሪያ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ የሠጠውን ውሣኔ ፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሻሩ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ እልባት ያገኝ ዘንድ ይህ የሠበር ችሎት ለቦርዱ ሠጥቶ የነበረውን መመሪያ መረዳት ተገቢ ነው፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 13-10-98

የሰበር ሰሚው ችሎት በውሣኔው ቦርዱ በመደበኛ ፍ/ቤቶች በሚሠራባቸው የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች ሣይወሰን የተሻለ መስሎ በታየው በማናቸውም ዘዴዎች ተጠቅሞ አግባብ ነው በሚለው በማናቸውም አካሄድ ውሣኔ ላይ መድረስ የሚችል መሆኑ በአ/ቁ/42/85 የተመለከተ ቢሆንም ቦርዱ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ የሰጠው ውሣኔ በአመልካች በቀረበ የውሣኔ ይታረምልኝ ጥያቄ መልስ ሰጪን ሣይጠራና ሣያከራክር ውሣኔ መስጠቱ በአዋጁና በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠውን የመደመጥ መብት የጣሠ በመሆኑ ቦርዱ ግራ ቀኙ ባለበት ጉዳዩን በድጋሚ አይቶ እንዲወስን ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው ለቦርዱ የተላለፈው መመሪያ ምንም እንኳን ቦርዱ በአመልካች በቀረበው የውሣኔ ይታረምልኝ ጥያቄ መሠረት ጉዳዩን አይቶ ተገቢ ነው የሚለውን ውሣኔ ለመስጠት የሚያመለክተውንና ተገቢ ነው የሚለውን አካሄድ ሊከተል ቢችልም ውሣኔ ላይ ከመድረሱ በፊት ግን የአንዱን ወገን ብቻ ሣይሆን የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ መሆን እንዳለበት አዋጁም ሆነ ህገ መንግሥቱ ስለሚያስገድዱት የሁለቱንም ክርክር ሰምቶ የመሰለውን እንዲወስን ነው፡፡ በመሆኑም ቦርዱ አከራክሮ እንዲወሰን ጉዳዩ በመመሪያ የተመለሰለት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ ብቻ ሣይሆን ዋናውን ጉዳይ ጭምር ነው፡፡ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ እንደገና እንዲያይ የታዘዘ ፍ/ቤትም ሆነ በተያዘው ጉዳይ ቦርድ ደግሞ በትዕዛዙ መሠረት ሊፈጽም እንደሚገደድ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/343/2/ ያስገነዝባል፡፡ ስለሆነም ቦርዱ እንደገና እንዲያይ በተላለፈለት መመሪያ መሠረት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ውሣኔ መስጠት ህግ የጣለበት ግዴታ በመሆኑ አመልካችና መ/ሰጪን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ ውሣኔ በመስጠቱ የፈፀመው ስህተት የለም፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 13-10-98

በዚህም ምክንያት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቦርዱ የሥነ ሥርዐት ግድፈት ካለ ብቻ እርምት እንዲያደርግ እና ከሌለው ዋናውን ጉዳይ ማረም ሣያስፈልግ መዝገቡን እንዲዘጋ የሰጠው ውሣኔ የሰበር ችሎቱን ውሣኔ ያላገናዘበ ነው።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/1173 ሐምሌ 12/1997 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
2. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የካቲት 5/1996 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል።
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ወ/ፊ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ______ ቀን 13-10-98